# ★ዴሞክራሲያ★

****************************************************

*የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ዴሞክራሲያዊ) ልሣን*

****************************************************

ቅጽ 34 ቁ 2 የካቲት 2001 ዓ. ም


## ኢትዮጵያችን

የሦስት ሺህ ዘመን ታሪክ የሚወራላት፤ ተፈጥሮአዊ ተሥኀቦ ያላትና ጥንታዊ የታሪክ ቅርስ ባለሀብት የሆነች፤ ኢትዮጵያችን ናት። ወራሪና ቅኝ ገዥ ባዕዳንን ተከላክላ፤ ነፃነቷን ጠብቃ፤ ለሁሉም ጥቁር ሕዝብ የነፃነት ተምሳሌት የሆነች የምሥራቅ አፍሪካዊቷ ሀገር ኢትዮጵያችን ናት። ሁለቱንም ታላላቅ ሃይማኖቶች በቀዳሚነት ተቀብላ እስላሙም ክርስቲያኑም ኅብረተሰብ ተፈቃቅዶና ተቻችሎ የኖረባት ሀገር ኢትዮጵያችን ናት። ለሀገሩ ሉዓላዊነትና ለአንድነቱ ግንባሩን ለጥይት፤ እግሩን ለጠጠርና ለሾህ የሰጠ ጀግና አፍርታ በደምና በአጥንት ድርበሯን ያስከበረች ብቸኛ የጥቁሮች ሀገር ኢትዮጵያችን ናት። የተለያዩ ጎሣዎችን አካታ፤ በተለያዩ ባህሎች አሸብርቃ፤ የራሷ የተለያዩ በዓላት ያላት ሀገር ኢትዮጵያችን ናት። ቅድመ የሰው ልጅ መገኛ በመሆኗ፤ ዓለም በቅድመ ሰው ልጅ አኗኗርና ሥልጣኔ ምርምሩ ትኩረቱን የጣለባት ሀገር፤ የአፋሯ ድንቅነሽ ያስመሰከረችላት ኢትዮጵያችን ናት። ገና በአግባቡ ተጠንተው ያላበቁ ጥንታዊ የታሪክ ቅርሶቿ፤ የአክሱም ሥልጣኔ፤ የላሊበላ ቤተ ክርስቲያኖች፤ የጎንደሩ ፋሲለደስ ግቢ፤ የሐረሩ ግንብ፤ የኦሮሞው ገዳ ሥርዓትና በርካታ ሌሎች ምሳሌዎች ያቆዩልን መረጃዎችና ገና ሚስጥረ-ኢትዮጵያዊነታቸው እየተጠኑ ያሉባት አፍሪካዊት ሀገር ኢትዮጵያችን ናት። የራሷ ፊደል ባለቤት ሆና የሕዝቧን ጥንታዊ ገድሎች በቋንቋዎቿ ለታሪክ ያኖረች ሀገራችን ኢትዮጵያ ናት። እርግጥም፤ ኢትዮጵያዊነት የታሪክ ባለቤትነት ነው፤ ኢትዮጵያዊ ኩራት ነው።

ገና የሀገር ነፃነት በአፍሪካ ውስጥ ደብዝዞ በነበረበት ወቅት የራሷ አስተዳደርና መንግሥት የነበራትና በዓለም መንግሥታት ዘንድ እንደ ሀገርና እንደ መንግሥት እኩል የተሰለፈች አኩሪ ሀገራችን ኢትዮጵያችን ነች። ነፃነቷን ጠብቃ ለሌሎች የአፍሪካ ሀገሮች ነፃነታቸውን እንዲቀዳጁ ከፍተኛውን ሙግትና ትግል በዓለም አቀፍ ደረጃ ያደረገችና ለዛሬ ነፃነታቸው ከፍተኛውን ድርሻ ያበረከተች ሀገር ኢትዮጵያችን ነች። በሊግ ኦፍ ኔሽንስ ውስጥ በሙሉ አባልነት የተቆጠረችው ብቸኛዋ አፍሪካዊት ሀገር ኢትዮጵያችን ነች። ከአፍሪካ

የመጀመሪያዋ የዓለም ሰብዓዊ መብት ፈራሚ ሀገር የሆነችና ለአፍሪካ አንድነት ድርጅት መመሥረት ዋነኛዋ ኃይል የነበረች ሉዓላዊነት ሀገራችን ኢትዮጵያ ነች። ዛሬ እነኝህንና ሌሎች ብዙ ደግ ደግ የሀገራችን መታወቂያዎች ተረስተውና ተዘንግተው፣ በሌሎች አሉታዊ ሁኔታዎች ብትታወቅም፣ ይህ ውብ ገጽታዋ ለትውልድ ይተላለፍ ዘንድ ብዙ ሕይወት ተከፍሎበታል። ሀገራችን አንድነቷን፣ ነፃነቷንና ሉዓላዊነቷን ጠብቃ ትኖር ዘንድ ልጆቿ በጀግንነት ደማቸውን አፍሰዋል፣ አጥንታቸውን ከስክሰዋል። ሰው ሊኖር ሰው ሞቷል፣ ሀገር ልትኖር ጀግኖች አፈር ለብሰዋል።

ዛሬ ሀገሪቱንና ሕዝቡን እያመሰ ያለው ዘረኛና አሸባሪው የህወሓት ቡድን ሥልጣን ላይ እስከወጣበት ጊዜ ድረስ የተፈራረቁት አፄዎችና ገዢዎች በአስተዳደራቸው በደሎች ይወቀሱ ይሆናል እንጂ በሀገር አንድነት ላይ ፈጽሞ ሊነቀፉ አይችሉም። አፄ ቴዎድሮስ በመቅደላ፣ አፄ ዮሐንስ በመተማ፣ አፄ ምኒሊክ በአድዋ በሀገራቸው ጉዳይ አንደ መሪነት ብቻ፣ እንደ አፄነት ብቻ ሳይሆን እንደ ተራው ሕዝብ አብረው ተጉዘዋል፣ አብረው ተዋግተዋል፣ አብረው ደማቸውን አፍሰዋል። ይህን ክቡር ሀገርን የመጠበቅ ጀግንነት ያስመሰከሩት በመሣሪያ ኃይልና በጉልበት ሳይሆን በሕዝብ አንድነት ነበር። ሀገር ሲባል ከደቡብ ሰሜን፣ ከምዕራብ ምሥራቅ ወደ ድንበሩ ለመሮጥ እሽቅድምድሙ ይበዛል። ጠላትን ለማነቅ ቀዳሚ አለመሆን የርግማን ያህል ይሆናል፣ ያሳፍራል። ያ ትውልድ ለሀገርና ለሕዝብ በሚከፈለው መስዋዕትነት ትውልድና ሀገር ለዘላለም እንደሚኖሩ አውቆታል። አንዱ ከአንዱ እየተማረ፣ አዲሱ የጥንቱን እየተከተለ፣ ይህ ትውልድ ከዚያ ትውልድ እየወሰደ፣ ሀገራችን በሀገርነቷ ትኖር ዘንድ ጥረዋል። ያለፈው ሲሄድ፣ ይህ ትውልድ ያ ሲሆን፣ ሀገር ግን ሁሌም ኢትዮጵያ እንድትሆን የዘመን ግዳጃቸውን ተወጥተዋል፣ ለዚህም ታሪክ ሲያስታውሳቸው ይኖራል።

ሆኖም ግን፣ ይህን ሁሉ የሀገራችንን በጎ ገጽታ ስናወሳ ሕዝባችን እየተጠማ፣ እየተራበ፣ እየታመመና እየተበደለ በጨቋኝ የገዥና የተገዥ ሥርዓት ውስጥ ሲኖር እንደነበረ በመዘንጋት አይደለም። የመከራ ገፈት ቀማሹ ሕዝብ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየበዛ፣ የገዥው ክፍል የኑሮ ሁኔታ ልቅ እያጣና ከሕዝብ እየተለየ፣ በኅብረተሰቡ ውስጥ የጎላ የመደብ ልዩነት እየሰፋ፣ በጎሣና በብሄረሰቦች መሃል ልዩነቶችና መራራቆች እየበረከቱ የሀገራችንና የሕዝባችን የወደፊት ዕጣ የማያስተማምንበት ደረጃ ላይ እየደረሰ መጣ። አፄያዊው አገዛዝ ኢትዮጵያን ከነበረችበት ኋላ ቀር የዕድገት ደረጃ ከፍ ለማድረግ ከመጣር ይልቅ ሥር በሰደደ ባላባታዊ አገዛዝና ስግብግብነት ሀገርን አዳክሞ፣ ሕዝብን ደቁሶ ረሃብ መለያችን እንዲሆን አደረገ። ዓለምም ድህነትንና ረሃብን ከኢትዮጵያ ጋር አያያዘ።

የአፄውን የአገዛዝ ብልሹነትና ኋላ ቀርነት የተረዳው ተማሪው፣ ምሁሩ፣ አርሶ አደሩ፣ ሠራተኛውና ወታደሩ ወንድ ሴት ሳይለይ በአንድነት፣ አንድ ኢትዮጵያ፣ አንድ ሀገር፣ አንድ ሕዝብ ብሎ በንጉሡ አገዛዝ ላይ ዳር እስከዳር ተነሳ፡፡ የዛሬ 35 ዓመት፣ በየካቲት 66፣ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በንጉሡ አገዛዝ ላይ ሲያምጽ ለሀገሩና ለአንድነቱም ቅድሚያ እየሰጠ ስለ ሀገሩ እየዘመረና ሰንደቅ ዓላማዋን እያውለበለበ ነበር፡፡ የየካቲት አብዮት በእስላሙ፣ በክርስቲያኑ፣ በወታደሩ፣ በተማሪው፣ በምሁሩ፣ በከተሜው፣ በገጠሩ አንድነትና ትብብር ተበዳዩ ሕዝብ በበዳዩ አገዛዝ ላይ በአንድነት ያመጸበት፣ ለመብትና ነፃነቱ የተዋደቀበት እንጂ ሀገራዊ አንድነቱንና ብሔራዊ ሉዓላዊነቱን ለደቂቃም ቢሆን የዘነጋበት አብዮት አልነበረም፡፡ የየካቲት 66 አብዮት ሉዓላዊነቷና አንድነቷ በተረጋገጠች ኢትዮጵያ ውስጥ የዜጎቿ ሰብዓዊ መብት እንዲከበርና አጠቃላይ የዜግነት የፃነት እንዲረጋገጥ የኢትዮጵያ ሕዝብ በአንድነት መስዋዕትነት የከፈለበት አብዮት ነው፡፡ የአንዱን ክፍል ጥያቄ ሌላኛው ክፍል ደግፏል፣ በጋራ አስተጋብቷል፡፡ ሕዝባዊ ትግሉ በገዢው መደብ ከፋፍህ ግዛ ፖሊሲና አደናጋሪ ፕሮፓጋንዳ ፈሩን እንዳይለቅም በወቅቱ የነበሩ ተራማጅ ኃይሎችም የማይናቅ እገዛ አድርገዋል፡፡ በየካቲት 66 ሕዝቡ ለመሠረታዊ ለውጥና ለአዲስ ሕዝባዊ ሥርዓት ምሥረታ ያደረገው ትግል የባላባታዊውን ሥርዓት አናግቶና ነቅንቆ ለመጣል ችሏል፡፡ ነገር ግን፣ ሕዝባዊና ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመመሥረት የነበረው የሕዝቡ ትግል ፍላጎትና ምኞት በወታደራዊ አምባገነን ተቀጨ፣ ጭፍጨፋ ነገሠ፡፡

ኢትዮጵያዊነትና ሀገር በደርግ አምባገነናዊ አገዛዝ ሥር ትርጉማቸውን አጡ፣ ጨፍጫፊውን አገዛዝ ከመደገፍ ወይም ከመቃወም አኳያ ብቻ ታዩ፡፡ አገዛዙን የተቃወሙ ሁሉ በሀገር ጠላትነት ተፈረጁ፣ ለዴሞክራሲ መብት ድምጻቸውን ያሰሙ ወጣቶች ተፈጁ፣ ሕዝባዊ መንግሥትን የጠየቁ ታረዱ፣ እናቶች፣ አባቶችና ሕፃናት በሙታን ተከበቡ፣ ሞትና ቤተሰብ ተዳበሉ፣ ሀገር ተሸበረ፡፡ ሀገራችን ኢትዮጵያ በአሥር ሺዎች የሚቆጠሩ ብርቅዬና ጀግኖች ልጆቿን ያጣችበት ዘመን ሆነ፣ ቀይ ሽብርና ኢትዮጵያ በታሪክ ማኅደር በተያያዥነት ሠፈሩ፡፡

አግባብነት ያላቸውን የመብትና የእኩልነት ጥያቄ ያነሱትን ከሌሎች ባለመለዬትና ሁሉንም በገንጣይ አስገንጣይነት በመፈረጅ በአንድ ኢትዮጵያ ስም የኦሮሞ ልጆች ተጨፈጨፉ፣ በአንድ ኢትዮጵያ ስም የኤርትራ ወገኖቻችን አለቁ፣ በአንድ ኢትዮጵያ ስም የትግራይ ልጆች በጥይት ተለቀሙ፡፡ በሀገር አንድነት ስም ሕዝባችን ምንነቱን እንዲጠራጠር ሆነ፣ ሀገራችን ለባሰ የሀገር መከፋፈልና መበጣጠስ ተጋለጠች፡፡ ኢትዮጵያችን ከረሃብና ቀይ ሽብር ጋር ሦስተኛ ጓደኛ አገኘች፣ ጦርነት፡፡

በደልና ጭቆና ባሉባቸው የሕዝቡ አመጽና ትግል አይቀሬ ናቸውና የ17 ዓመቱ ፋሽሽታዊው ጽልመት በከባድ የሕዝባችን መስዋዕትነት ተገረሰሰ፡፡ "ትሻልን ችቼ ትብስን" እንዲሉ፣ የሀገራችን ዕጣ ዕድል ሆነና፣ የሕዝባችንና የሀገራችን አንድነት የሚያባንነው፣ የጥንት ታሪካችን መንቋሸሽ የሚያስደስተውና ኢትዮጵያዊነትን በነፍጠኝነት የሚተረጎመው ዘረኛና አሸባሪ የህወሓት መንግሥት አምባገነናዊውን ደርግ ተካ፡፡ ሕዝብን ከሕዝብ ለመለየትና ለማጨራረስ ወደ ኋላ የማይል፣ የሀገርን ለም መሬቶችና የደን ሃብቶችን አሳልፎ ለባዕዳን የሚሰጥ፣ ያለ ምንም ይሉኝታና ብሔራዊ ስሜት ዳር ድንበርን የሚያስደፍር፣ ሀገሪቱን ወደብ አልባ አድርጎ ፍጹም ድኅነትን በአገሪቱ የማያባራ፣ በሎሌነት ለሌሎች ያደረና ሊታዘዝም የመጨረሻ ውጤቱ ሀገራችንን ሊጎዳ በሚችል ድንበር ዘለል የወረራ ጦርነት የኢትዮጵያ ልጆችን የሚያስፈጅ፣ አልመቸው ሲል ደግሞ ሀገሪቱንና ሕዝቡን በትኖ ለመጠፋት ሕገ-መንግሥትን የሚጽፍ ጉደኛ መንግሥት በኢትዮጵያ ሕዝብ ጫንቃ ላይ ተደላደለ፡፡

እኛ ኢትዮጵያችን ስንል ድንበር ዘላ ወረራ የምታካሄደውን ኢትዮጵያ አይደለም፡፡ እኛ ኢትዮጵያችን ስንል የኦሮሞ የጋምቤላና የአጋዴን ወገኖቻችንን በጅምላ እየተጨፈጨፉ ያለባትን ኢትዮጵያ አይደለም፡፡ እኛ ኢትዮጵያችን ስንል በፖለቲካ እምነታቸው ብቻ እልፍ አዕላፍ በየእሥር ቤቱ እየማቀቁ ያሉባትን ኢትዮጵያ አይደለም፡፡ እኛ ኢትዮጵያችን ስንል ሁሉም ኢትዮጵያዊ ዜጋ በጋራና በእኩልነት የሚኖርባት፣ የሁሉም ዜጎቿ ባህልና ቋንቋ ታውቆና ተከብሮ የሚኖርባት፣ ሁሉም በሀገሩ ጉዳይ ውስጥ ዘር፣ ፆታና ሃይማኖት ሳይለይ እኩል መብት የሚጎናጸፍባትና የወሳኝነት ሚና የሚጫወትበትን ኢትዮጵያ ማለታችን ነው፡፡ እኛ አንድነት ስንል መብትና ነፃነት ያገኘን ሕዝብ ማለታችን ነው፡፡ እኛ የሀገር አንድነት ስንል የዚያ አንድነት አስጠባቂ አገዛዙ ሳይሆን እራሱ ባለመብቱ ሕዝቡ ነው ማለታችን ነው፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ዴሞክራሲያዊ) ለኢትዮጵያ አንድነትና ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መስፈን ሁሌም ይታገላል፡፡ ሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶችም ለዚህ ዓላማ በጋራ እንዲታገሉ ይጥራል፡፡ የየካቲት 66 ሕዝባዊ አብዮት በውል ያስመዘገበውን ሕዝባዊ የትግል አንድነትን መሠረት አድርገን ሀገራችንና ሕዝባችንን ከባሰ አደጋ ለማዳንና የተሻለ ብሩኅ ቀን ለማየት በጋራ የጋራ ጠላታችንን ለማስወገድ መቻል ይኖርብናል፡፡ ለዚህም እንደ ጥንቱ "አንድ ሀገር አንድ ሕዝብ" ብለን መነሳት ብሔራዊ ግዴታ መሆኑን ኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) በአጽንዖት ያሳስባል፡፡ የሀገራችንና የሕዝባችን አንድነት ለወደፊቱ ሀገራዊና አካባቢያዊ መረጋጋትና ሠላማዊ ኑሮ የመጀመሪያው አስፈላጊ ጉዳይ መሆኑ ኃላፊነት ለሚሰማቸውና ሕዝባቸውን ለሚያከብሩ የፖለቲካ ድርጅቶች ግልጥ

ይሆናል ብለን እንገምታለን፡፡ በኛ እምነት ከአንድነት ውጭ የሚኖው አማራጭ ውጤቱ ዘግናኝና ከቶውንም ሊታሰብ የማይገባው፣ የሕዝብ መተላለቅና የጦርነት ገሃነም ይሆናል፡፡ ለመግዛት ካልተቻለው የህወሓት መንግሥት በአዘጋጀው ሕገ-መንግሥት መሠረት ሀገሪቱን በትኖ ሕዝባችንን በዘላለማዊ የጦርነት ገሃነም ውስጥ ለመክተት መዘጋጀቱን የኢትዮጵያ የተቃዋሚ ድርጅቶች የሚስቱት አይመስለንም፡፡ ሆኖም ግን፣ ሀገርንና ሕዝብን ከዚህ አደጋ ለማትረፍ ሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች ያለባቸውን የታሪክ ግዴታና ኃላፊነት ደጋግሞ ማስገንዘቡ ደግሞ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ ሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች ኃላፊነት ተሰምቷቸው የህወሓትን ተንኮሎች በጋራ ለማክሸፍ የየግል የፖለቲካ ፍላጎቶቻቸውንና ምኞታቸውን ይሁን በመካከላቸው ያለውን ጥላቻ ለዚህ ታላቅ ብሔራዊ አጀንዳና ጥሪ ተገዥ ካላደረጉ የወደፊት ዕድላችን ይህን ያህል አያስጎመጅም፡፡ ስለዚህ፣ የፖለቲካ ድርጅቶች በመካከላቸው ያሉትን መለስተኛ ልዩነቶችን ለዓመታት በጭቆና፣ በረሃብ፣ በበሽታና በድንቁርና እየተገረፈ ላለው ሕዝባቸው ሲሉ ወደ ጎን አድርገው፣ በሕዝቧ እኩልነት ላይ የተመሠረተ ሀገራዊ አንድነትና ብሔራዊ ሉዓላዊነት እንዲከበር፣ የዜግነት ሙሉ መብቶችና የሕግ የበላይነት ኢትዮጵያችን ውስጥ እውን እንዲሆን በጋራ ለጋራ ዓላማ እንዲቆሙ ኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) ጥሪውን በድጋሚ ያቀርባል፣ የበኩሉን ጥረት ይቀጥላል፡፡ በዚህ ረገድ ሀገር ውስጥ በሕጋዊነት እየተንቀሳቀሱ ያሉ ስድስት የኢትዮጵያ የተቃዋሚ ድርጅቶች በመሰባሰብ የምክክር መድረክ መፍጠራቸውና አሁን ደግሞ ቀደም ብለው ካልተካተቱት ድርጅቶች ውስጥ አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ የዚህ መድረክ አባል ለመሆን መወሰኑ እጅግ አስፈላጊና ወሳኝ ለሆነው ሁሉን አቀፍ ኅብረት ምሥረታ ለሚደረገው ጥረት መልካም ጅማሮ ነው፡፡ በሀገሪቱ ውስጥ ሕጋዊነትን ተከልክለው በህቡዕ ለመንቀሳቀስ የተገደዱና በተለያዩ ቦታዎችና አካባቢዎች ሆነው በመደራጀትና በመታገል ላይ የሚገኙት ፓርቲዎችና ድርጅቶችም ተመሳሳይ እርምጃዎችን በመውሰድ የኅብረት ፈጠራውን ሂደት ለማጠናከር ፈጥነው መነሳት እንደሚኖርባቸው ወቅቱ ያስገድዳል፡፡

በሕዝብ አንድነትና እኩልነት ላይ የተመሠረተች ኢትዮጵያ!
የዜጎች ሰብዓዊ መብት የተከበረባት አንድ ኢትዮጵያ!
ኢትዮጵያ በልጆቿ አንድነትና ቆራጥነት ተከብራ ትኖራለች!